# የትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ካርድ /yellow ID card / የማውጣት ሂደትና የ40/60 የቤት ስራ ምዝገባ አካሔድ እያስከተለው ያለው ውጥንቅጥ

*ከቅንነት ይበጃል*

## መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት የትውልድ ኢትዮጵያዊነት መታውቂያ ካርድ በውጭ ሃገር ላሉ ትውልደ ኢትያጵዊያን ሊሰጥ ሲያስብ ውጭ ሃገር ያለው ዜጋ የበለጠ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲሰማውና በሃገሩ የልማት ፤ የኢንቨስትመንትና መንግስት በዘረጋቸው መላ ተግባሮች ሁሉ ባይታዋርነት ሳይሰማው እንዲሳተፍ በማሰብ መሆኑ አሌ የማይባል ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ሰዓት በ40/60ና በማህበር ቤቶች ትውልደ ኢትዮጵያዊው በማህበር ተደራጅቶ የግንባታው ተጠቃሚ እንዲሆን መንግስት በስፋት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ። ይህ እንቅስቃሴ ይበጅ የሚያሰኝ ቢሆንም የአሰራሩ ሂደት ግን ተዘናፋነት ፤ መንግስትንና ህዝብን በማንነቱ ለማብጠልጠል የሚያመችና ከዚያም አልፎ የሚጠየቁት መመዘኛወች ሳይታሰብበት፤ ወይም በዘፈቀደ ሰወች በራሳቸው አስተሳሰባዊ ስሜት እየተገፋፉ እያደረጉት ይሆን ባይታወቅም ነገ ተጠያቂነትን ስለሚያመጣ ከወዲሁ መላ እንዲባልለት በማሰብ ይህን አቤቱታ የሰሚ ያለህ በማለት ለማቅረብ ተገደናል።

## እየተከሰተ ያለው ውጥንቅጥ

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የተዘረጉ መልካም ጂምሮች በተዘረጋው የአሰራር ሂደት መፋለስ፤ ኢትዮጵያዊነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው በሚል ግለሰባዊ የፍርደ ገምድል ፈሊጠ ህሳቤ እግዚሐብሔር መርጦ የሰጠንን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ለማጣራት የሚዳዳቸው የሚጠይቁን አካልትና ግለሰቦች ተፈጥረው ለፈተናና በዘመናት ታይቶ የማይታውቅ ውርጅብኝ ተጋርጦብናል።

በአንድ በኩል ለፈጣሪ “አትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብር ዥጉርግርነቱን አይለቅም” ሲል ታላቁ መፅሐፈ ቅዱስ ሆነ ቁርሃን ስለአተተው ለሱ ለፈጣሪ መላ እንዲለን እንዲሁም በሌላ በኩል ለመንግስት እንዲያውቀው ከሩቅ ሃገር ሁነን እግዝኦ / አላህ ወአክብር / ብለን እንጮሃለን።

ጉዳይን የሚያጣሩት ቡድኖች ፤ አካልና ግለሰቦች በፈጠሩትና ራሳቸው በዘረጉት የማስፈፀም ሃካሄድ ችግሮች፤ ውጥቅጦችና  የተመቻቸው መልካም የመንግስት ስናይ ህሳቤ እርስበርሱ እየተጋጩ በአብዛኛው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ላይ

መደናበር፡ ራስ ምታት፤ መያዣ መጨበጫና ውል ያጣ ጉዳይ እየሆነበት ይገኛል። ዜጋው መንግስት ሊሰጥ ያሰበው የቤት መስራት እድል ተጠቃሚ ለመሆን የቢጫ ካርድ እንደሚያስፈልገው በመመዘኛነት ማስቀመጡ ካለው ተጨባጭ እውነታዊ ክስተት ጋር አስፈላጊነቱ አሌ የማይባል ጉዳይ መሆኑ የሚደገፍና የሚያስኬድበት ሁኔታ እንዳለ እንቀበላለን።

መንግስት ሆነ አስፈፃሚ አካላት የምዝገባና የኢትዮጵያዊነትን ማንነት የማጣራቱን ስራ በዲያስፖራ ለሚገኙ የልማት ማህበራትና መሰል ተቋማት በመስጠት ስራውን በቅንነት ለማካሄድ ማሰቡ የሚደገፍ ቢመስልም ተቋማቱ ያልተመልከቷቸው ህፀፆች እየታዩ ስለመጡ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው እያሳሰብን ማሳሰቢያችን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

በውጭ ሃገር የኢትዮጵያዊያንን መላ ምልሁ የብሄር ብሄር ማንነታችንን፤ ብዝሃነታችንና እኛነታችን ወክለው የተድራጁ ማህበራት ስለሌሉ እንዳለፈው ስረዓት የብሔር ብሔረሰብ አባላት በውሸት ጉዳቱንና የነገውን ጣጣ ሳያገናዝቡ ማንነታቸውን በጥቅም ተገደው ለመለወጥ ሲዳዱ እየታየ በመሆኑ ።

የእንግሊዝ ፤ የአሜሪካና የአውሮፓ ፓስፖርታቸውን ያያዙ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የትውልድ ቦታቸው እስከተወለዱበት ቀየ ድረስ ኢትዮጵያዊ ሸዋ ፤ ጎንደር ፡ ጎጃም ፤ አዌ ዞን ፤ ወለጋ ፤ ወላይታ ሌላም በሚል ታትቶ ሰፍሮ እያለ የኮሚኒቲ ተወካዮች በተለይ የነፍጠኝነት ስሜት ያለቀቃቸው የአማራው ተወካይ ነን ተብየወች ማን እንዳዘዛቸው ባልግባን መልኩ ቅን የአማራ ልጆች ተው እያሉና አካሄዳቸው እንደማይዋጣ እየመከሩ በማን አለብኝነት ግለሰቦች አዲስ አበባ ና መሰል ቦታወች በመወለዳቸው ብቻ ወጣት እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ማንነታቸውንና ከቤተሰቦቻቸው የወረሱትን እነሱነታቸውን "አማራነትህንና ኢትዮጵያዊነትህን አስረግጥ በሁለት ምስክር" እየተባለ ውስጣዊ ስሜታቸው ባልተቀበለው መልኩ የስራውን ሂደት ለማከነወን መዳዳቱ ህሊናን የሚቆጠቁጥ ፤ የተወካዩ አማራነት፤ ዓላማና ማንነት ሊፈተሽና መላ ሊባልለት ይገባል እንላለን ።

ልማት ማህበሮችም በየሃገሩ ቻርተርና ቻሪቲ ሕግ የሚተዳደሩ በመሆኑ ከቀሙበት ዓላማ አንፃር ከፖለቲካ፤ በሃይማኖትና በዘር ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ እያተተ ይህን ውል ረስተው ሃገራዊ ማንነትን ይባስ ተብሎ ታላቁን ባለመታውቂያ ኩሩ በውጭ ወራሪ ያልተደፈረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጎብዳጆችና የኢትዮጵያዊነት ውል በሌላቸው ግለሰቦች "ኢትዮጵያዊ ነህ ሆይ" ብሎ ከመጠየቁ አልፎ በሁለት ምስክር አምጥተ ኢትዮጵያዊነትህን አስመስክር ብሎ መጠየቀ አጿሂብ የምያሰኝ አሳፋሪ ፤በወራራው ዘመን ጠላት ካደረገው ድፍረት የማይተናነስ ተንኮል ጥንስስ ሴራ በመስራት ላይ መሆኑን ልንገልፅ እንወዳለን ።

ሃገሬ ሞኘ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደልሽ በላ" የሚለው የተለምዶ አባባል ዘመኑ ያስረጀው አባባል ቢሆንም

ዛሬ ግን ጊዜና ዘመን አያመጣው የለ

"ዘመን መንገድ የለው
ሩቅ መዳረሻ ዱካው፣

ኢትዮጵያዊው አሳቻ ላይ ቆሞ
ይጠየቀው ጀመር አንተ ማነህ ብሎ

ማተብ፤ ማንነት ተረስቶ
ዘመን ከሰው ልቆ"

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ዲሞክራሲን የምትከተል ሃገር በመሆንዋ ለስደት ተዳርጎ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በጥገኝነት እጁን በሰጠበት በምዕራቡ ዓለማት የመኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት ሲል ኢትዮጵያዊው ኤርትራዊ ኢንዲሁም ሱማሌ ነኝ በማለት ማንነቱንና ስሙን ለመለወጥ የሚያስገድዱና በዚህ አካሄድ የመኖሪያ ወረቀት እያገኘ እንደሆነ የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል።

በተለያዩ ዓለማት ውስን የልማት ማህበራት ይገኛሉ እነሱም የትግራይ ልማት ማህበር፤ የአማራ ልማት ማህበር ፤ የደቡብ ህዝቦችና የሱማሌ ዲያስፖራ ማህበራት የሚባሉ እንዳሉ ከቻርተርና ከቻሪቲ ኮሚሽን በደረሰን መረጃ ለማረጋገጥ የቻልን ሲሆን እነዚህ የልማት ማህበራት መላውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች አባላት የማይወክሉና ካላቸው ቅርበትና ቀድሞ ከመሰደድ እንዲሁም የብሄረሰቦቹ ቁጥር ብዛትን ተንተርሰው የተመሰረቱ እንደሆኑ ይታወቃል።

የትግራይ ማህበራት ትግረኛ ተናጋሪው በቋንቋው ተማስሎነት ና ከቶዳ ስፋቱ አንፃር ማን ማንነቱን ለማወቅ የማያስቸግር ቢመስልም ብዙው የትግራኛና ትግረ ተናጋሪው ኤርትራዊ ነኝ በማለት ኢትዮጵያዊ ማንነቱን የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ሲል ስለለወጠ ኤርትራዊ እንግሊዛዊ ለመሆን የተገደደው የትየ ለሌ ነው ።

አንዳንዱም መንግስት ሰሞኑን የዘረጋው እድል ተጠቃሚ ለመሆን ሲል ኢትዮጵያዊ ነኝና የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊነቴ ተገልፆ የቢጫው ካርድና የቤት መስሪቱ እድል ተጠቅሚ ልሆን እችል ዘንድ የትብብር ደብዳቤ ይፃፍልኝ ብሎ ማመልከቻ ስያቀርብ አናውቅህም የሚል ምላሽ ሲያገኝና መንቀሳቀሻ ሲያጣ ይታያል ።

ዞር ብሎ ደግሞ አማራ ነኝ የመኖርያ ፍቃድ ላገኝ ስል ማንነቴን ለወጥቅኩ እንጂ በማለት ማንነቱን ለጥቅማጥቅም ሲል "አያ በሬ ሆይ ሳሩነን አይተህ ገድሉን ሳታይ" እንዲሉ የተለያዩ የተዘበራረቁ ሁኔታወች ላይ ትውልደ ኢትዮጵያዊው ተፈጥሮበታል።

አይ ዘመን አንዲል እነዘርዓይ ድረስ ፤ አብርሃ ደቦጭ ፤ አብዲሳ ሃጋና መሰል የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ኢትዮጵያዊነታቸውን ባስመሰከሩበት ምድር በጥቂት ኢትዮጵያዊ ነን ተብየ ሆዳም ጁቢራወች ኢትዮጵያዊነቱን ትውልደ ኢትዮጵያዊው እንድያስመሰክርና ማንነቱን ለመሸርሸር መሞከሩ ጎራዴ ሳይማዝዝዝና የታሪክ ጠባሳ ጭሮ ሳይሄድ መላ ሊባልለት ይገባል እንላለን ።

ኢትዮጵያ የሰማኒያ ብሄር ብሄረሰቦች ሃገር ስትሆን ለመስተዳደር አመችነትና አቅርቦታዊ ዝምድናን መሰረት አድርጎ በአማራ ፤ በትግራይ በኦሮሚያ፤ በደቡብ ሕዝቦችና ብሔር ብሄረሰቦች ፤ በቤንሻጉል ፤ በጋምቤላ ፤ በአፋር፤ በሃረሬና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ተካልላ የምትገኝ ሃገር ናት ።

በውጭ ሃገር ያሉት የብሔር ብሄረሰብና የክልል ዲያስፖራ ማህበራት የተወሰኑ በመሆናቸው በአጋጣሚ ሆኖ የኦሮሚያ ፤ የሃረሬ ፡ የጋምቤላ ፤ የቤንሻጉል ፤ የሃፋር ብሔረሰብ አባላት የቢጫ ካርድ ለማግኘት ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚገልፅ መርጃወች ሊኖራቸው አይችልም የሚል ግምትም ሆነ በሌላም ሁኔታ ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሚሆንበት ሁኔታ ቢፈጠር ቀለል ባለ መልኩ፤ በውስጥ አሰራር፤ በሚያመችና ተፅህኖ በሌለበት ሁኔታ ሊሆን ይገባል እንላለን።

ነገር ግን የተከፈተውን አጋጣሚ በመጠቀም አማራ ያልሆኑትን አማራ ኢትዮጵያዊ እንዲባሉ የሚያስገድዱ ያልሆኑና ፈር የለቀቁ አካሔዶች እየተከሰቱ በመሆኑ ይህ በአደባባይ የሚከናውን አሰራርና አካሔድ ብዙውን ኢትዮጵያዊ እንዳለፈው ዘመን በግድና በጊዚያዊ ጥቅም አማራ እያደረገውና ማንነቱን፤ ራሱን እንዲያጣና ወደፊት የሚያስከትለውን ችግር ያላገናዘበ ፤ መንግስትን የሚያስውቅስ ፤ ወደድሮው ስረዓት የሚጎተትን፤ ለሃሜትና ለአሉባልታ የሚያጋልጥ በመሆኑ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የግድ የሚል ሆኖ አግኝተነዋል።

ኢትዮጵያዊነትን በሌላ ኢትዮጵያዊ እያስመሰከሩ የስራው ሂደት እንዲከናወን የሚያደርጉ የኮሚኒቲ መሪ ነን ባዮች ኢትዮጵያዊነትና የውክሉት ብሄረሰብ አባልነታቸው ስለሚያጠራጥር ካልበሰለው እንጭጭ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እንመክራለን።

ከዝህ ሌላ ይህን ጉዳይ እንዲከታተሉና እንዲያስፈፅሙ የተመደቡ የየብሔረሰቡ ተወካዮች ኢትዮጵያዊው ኢትዮጵያዊነቱን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴወችን መጠቀም ሲገባቸው ሁለት ምስክር አምጡ ብሎ በአደባባይ መጠየቁና ያስፈልጋል

የሚባለው ፈሊጥ በእውነት ዘይገርም የሚያስብል ፀረ ኢትዮጵያዊነት ፤ ራሳቸው አስፈፃሚዎች የትላንት ማንነታቸው እየታወቀ ይህን ከባድ ስራ ኢንዲያከውኑና ህፀፃዊ ሳይታሰብበት እየተሔደበት ያለው አካሄድ የኛን መልካም ከማያስቡ ብዱኖችና ግለሰቦች ጀሮ ገብቶ የአንድሰሞን መዛበቻ እንዳንሆን መንገዱን ማመቻቸቱ አስፈላጊ ስላልሆነ ከወዲሁ ይህ አካሔድ ሊቆምና እንደገና በጥሞና ሊፈተሽ ይገባል የሚል አሳብ እየተንሸራሸረ ይገኛል።

ተውክሎ የተቀመጠው አስመስካሪ የየብሔረሰቦቹ የልማት ማህበር ተወካይ ቢያንስ ቢያንስ ትውልደ ኢትዮጵያዊውን የሚያውቅ ፤ በዘየው፤ በብዓሉ፤ በቋንቋው፤ በኢትዮጵያዊ ቀናይነቱና ሌሎች ዘና ያሉ አካሄዶችን በመጠቀም መተባበር ሲገባቸው ህብረተሰቡ የብሔረሰብ መገለጫውን፤ የሚኮራበት ማንነቱን ወደ ሚገፍና ወደ ከፋ አካሄድ የሚያስጉዝ ይህ አይነቱ ኢ-ሕገመንግስታዊ አካሔድ ሊቆም ይገባል።

መንግስት የቢጫ ካርድ ትውልደ ኢትዮጵያዊው ኢንዲያገኝ የትብብር ደብዳቤ ይፃፍለት ብሎ ቀናነቱን አሳየ እንጂ ከላይ የተዘረዘሩት ውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ የልማት ማህበሮችና ተቋማት እንዲገቡ መልእክት ያለአስተላለፈና ፍላጎቱ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። መጣራት የሚያስፈልግ ጉዳይ ካለ የበላይ አካል ይህን መሰሉን የሃገር ደህንነትን የመጠበቁን ጉዳይ የሚያጣራበት ዘዴ ስላለው ከዚህ ውስብስብ ጉዳይ ላይ የማይመለከትው ቡድኖች ፤ ግለሰቦችና የኮሚኒቲ ተመራጭ መግባቱ ህግንና ህገ-መንግስቱን የሚጥስ በመሆኑ እጅን መሰበስብ ኢንደሚገባና ስህተቶች ካሉ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድና ከወዲሁ ሃገር ከሚጎዳ ጉዳይ እንዳይገባ በማለት በመላው ኢትዮጵያና በአትዮጵያ አምላክ ስም እንጠይቃለን።

ተገደው ወይም ለኑሮ ሲባል ኢትዮጵያዊነታቸውንና መጠሪያ ስማቸውን ወደ ጎን አርገው ኤርትራዊና ሶማሌ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን የተፈጠረው እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታወች በተጠና መልኩ መመቻቸት ያለበት ሲሆን ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ብሎ ማሸሸቱና ያልሆነ መስመር ተክትሎ ራሳቸውን እንዲያጡ ማድረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን መላ ሊበጅለትና በበሰለ መልኩ የሚስተናገዱበት ሁኔታ ቢመቻች እንላለን።

ከዚባሻገር በዚህ ክፍተት ሊፈጠር የምችለው ጉዳት ኢትዮጵያውያንን ከመጥቀሙ ባሻገር የእናት ጡት ነካሾችና ተባባሪወች ሰርገው የሚገቡበት ሁኔታ በዚህ አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል በግለሰቦች ከሚሰራ በጋራ ኮሚቴ ተዋቅሮ በሰከነ፤ ክፍተት በሌለበትና ከሰርጎገቦች በፀዳ መልኩ እንዲሰራና ጥናትን ተመርኩዞ ከዝህ በፊት የተደርጉት እፀፆች እንደገና ተፈትሸው የዕርምት እርምጃ እንዲደረግባቸው ከአደራ ጋር በታላቅዋ አትዮጵያ ስም የእትዮጵያ ልጆችን ወክለን እናሳስባለን ።

# ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ከሚደርሰን መረጃና ቅሬታ የሚከተሉት ክትትሎችና ማስተካከያዎች እንዲደረጉ አሳባችን እናቀርባለን ፣

1) የቢጫ ካርድ የማውጣቱ ስራ ብሔር ብሔረሰብን አካቶ መሰራቱ ባይከፋም እያንዳንዱን የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የሚወክል የዲያስፖራ ማህበር ስላልተዋቀረ ለጊዜው የተፈጠረውን እድል ለመጠቀም ሲባል የብሔር ማንነትን ለጥቅም ተብሎ የመለወጥና የመዋሸት ሁኔታ እየታየ ስልሆነ ይህ አካሔድ ኢንዲቆም ቢደረግ ፤

2) ለኑሮና ለመኖሪያ ፈቃድ ሲባል ኢትዮጵያዊነታቸውንና ስማቸውን ለጊዜው ገሸሽ አርገው ኤርትራዊና ሶማሌ አሜርካዊ ፤ኢንግሊዛዊና የሌላ ዜጋ የሆኑ  ትውልደ ኢትዮጵያዊያን አጣብቂኝ ሁኔታ ላይ መግባት የጠላት ሰለባና ጠላት ገብቶ ጉዳት ያመጣል የሚል ህሳቤ ቢኖርም የጉዳዩ አሳሳቢነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ በብስለት ቢኬድበት ፤

3) ትውልደ ኢትዮጵያዊውን አንጥረው የሚያውቁ፤ አቅም ያላቸውና የሚታየውን ክፍተት መድፈን የሚችሉ ሃገር ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን መዋቅሩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመማከር ስራው ቢከናወን፤

4) ኢትዮጵያዊነት በምስክርነት ለማስረገጥ  መዳዳቱ ከብቃት ማንስ የተነሳ በግለሰቦች ማናለብኝነት ስሜታዊ አካሔድ ታቅዶ እየተሰራ በመሆኑ ጉዳቱ ክፍተትን የሚፈጥር ፤ ኢ-አሉታዊ ክስተቶች ሳያመጣ እንዲወገድ አስቸኳይ የዕርምት ኢርምጃ ቢወሰድበት ይሻላል እንላለን፤

5) ትውልደ ኢትዮጵያዊው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትብብር ደብዳቤ ኢንዲፃፍለት የልማት ማህበራትና ሌሎች ተቋማት ከማድረግ በዘለለ አላስፈላጊ የኢምግሬሽንና ወንጀል ነክ የፖሊስ ስራ መስራት የኮሚኒቲ አባለት ተመራጮችና ተወካዮች መብትና ስራ ስላልሆነ ከድርጊታቸው ኢንዲቆጠቡና ለሰሩት ስራ ይቅርታና የእርምት እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወሰዱና ያለስራቸው እንደርጎ ዝንብ ጥልቅ እንዳይሉ እናሳስባለን።

"ኢትዮጵያና ልጆችዋ በክብር ካሰቡት ዳፋ ይደርሳሉ ፤ አንጠራጠርም !!!"

"ኢትዮጵያዊነት ቃል ፤ የልቦና ውርስ እንጂ በግለሰቦችና ምስክርነት የሚቸር አልባሌ ዕቃ አይደለም !!!"